# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ጥቅምት 27 ቀን 2003 ዓ.ም**

**ወያኔ በሪል እስቴት ስራ ከተሰማሩት ኢትዮጵያውያን ላይ መሬት መቀማት ጀመረ፤**

**ባለሀብቶቹ በወያኔ ግፍ ተፈፀመብን እያሉ ነው፤**

**የአባ ገብረመድህን ቀኝ እጅ የነበረው ሀገር ጥሎ ኮበለለ ተባለ፤**

**ሐውልቱ እንዳይፈርስ ውስጥ ውስጡን ስራ መስራት መጀመራቸው ተጋለጠ፤**

ወያኔ ኢትዮጵያውያን ኢንቨስተሮችን አዳክሞ የራሱ ተገዥ እና አጎብዳጅ ለማድረግ ከግዜ ወደ ግዜ የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀመ ሲሆን ሰሞኑንም በቤት ግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን መሬት መንጠቁ ታወቀ::

የመለስ አሽከር የሆነው እና የበረሀ ምርኮኛው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ሰሞኑን ድንገት በወሰደው እርምጃ ለብዙ ዓመታት በቤት ግንባታ ስራ ላይ የነበሩ ድርጅቶችን መሬት ቀምቶ መውረሱ ታውቆዋል::

ልዩ ግብረ ኃይል የሚል አንድ አፋኝ ቡድን አቁዋቁሞ ድንገት ሳይታሰብ በየቦታው እየተዘዋዙዋሩ በመገንባት ላይ የነበሩትን ድርጅቶች እና ገንብተው የጨረሱትንም ጭምር እየወረሰ ለወያኔ ገቢ ያደረገ ሲሆን በተለይ 40 ድርጅቶች ቤት ገንብተው ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ባሉበት ወቅት ተነጥቀው እንደተወሰደባቸው ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ገንዘብ ያለው ማንኛውም ዜጋ መስራት ይችላል ብሎ በአፍ እየለፈፈ ያለው የወያኔ ቡድን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ገንዘብ እየለገሱ ይቃወሙኛል ...... ለስልጣኔ ያሰጉኛል ብሎ የጠረጠራቸውን ባለሀብቶች እና ድርጅቶች ሰበብ አስባብ እየፈለገ ከስራ ውጭ ከማድረጉም በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች ባለቤቶቹን ለእስር እየዳረገ ሲሆን አሁንም ተመሳሳይ እርምጃ እየወሰደ መሆኑ ተጋልጦዋል::

ጥቅምት 22 ቀን 2003 ዓ.ም የተጀመረው መሬት መንጠቅ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ የቀጠለ ከመሆኑም ባሻገር ባለንብረቶቹ በአስተዳደሩ ጽህፈት ቤት ተገኝተው ሪፖርት እንዲያደርጉና አስፈላጊም ከሆነ ለእስር እንደሚዳረጉ የጠቆሙት የማዘጋጃ ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ለብዙ ዓመታት የወሰዱትን መሬት ሳይሰሩበት አጥረው ያስቀመጡ የወያኔ ደጋፊና አባል ባለሀብት ነን ባዮች ላይ አንድም እርምጃ ሳይወሰድ ስራ እየሰሩና ለዜጎች የስራ ዕድል የፈጠሩትን መሬት እየነጠቁ መውረስ መጀመራቸው ታውቆዋል::

በሀገሪቱ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ የሪል እስቲት ድርጅቶች ተቋዋቁመው ስራ የጀመሩ ከመሆኑም በላይ ከውጭ ሀገር ለሚመጡ ኢትዮጵያውያኖች የቤት ችግር እያቃለሉ የነበሩ ቢሆንም ወያኔ በራሱ ችግር ምክንያት ያለ ማስጠንቀቂያ መሬታቸውን እና የሰሩትን ቤት እየነጠቀ ገቢ እያደረገ መሆኑ በይፋ ተነግሮዋል::

የወያኔ ቀኝ እጅ የሆነው ሼህ ሙሀመድ አላሙዲን እጅግ ውድ ዋጋ የሚያወጣውን ፒያሳ አቅራቢያ የሚገኘውን የተንጣለለ ሜዳ አጥሮ ከያዘው 10 ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በእሱና መሰሎቹ ላይ አንዳችም እርምጃ ሳይወስዱ በቅርቡ ተመስርተው ስራቸውን በአግባቡ በሚወጡና የወያኔ ደጋፊ ያልሆኑት ላይ ይህንን መሰል እርምጃ መውሰዱ አስገርሞዋል::

ከፒያሳው በተጨማሪ በሜክሲኮ አደባባይ አጠገብ መሀል ቦታ ላይ እና በኢትዮጵያ ሆቴል አጠገብ በነፃ መሬቱን ወስዶ በቆርቆሮ አጥሮ እና ቀለም ቀብቶ እስከ ዛሬ ለ5 ዓመታት ያለ ስራ ያቆየው ቢሆንም እነ ኩማ ደመቅሳ ሳይናገሩት ለህዝብ እና ለሀገር የሚያስቡ ጥቂት ባለሀብቶችን ለማዳከም ብሎም ጭራሽ ከስራ ውጭ ለማድረግ ታስቦ ሰሞኑን መሬት መንጠቃቸው የሚያሳፍር እርምጃ ሲሉም በዚሁ የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ተቃውሞ እያሰሙ መሆኑ ተገልፆዋል::

ከተራ ነጋዴ ጀምሮ እስከ ትልልቅ ፋብሪካ ባለቤቶች ድረስ የወያኔ ደጋፊ ወይም አባል መሆን እንዳለባቸው እየተነገራቸው አንቀበልም ባሉት ባለሀብቶች ላይ ሰበብ እየፈለጉ ከንግድ እና ከስራቸው እያፈናቀሉ ባዶ እጃቸውን እያስቀሩዋቸው ከመሆኑም በላይ ዘመን አመጣሽ በሆነው ሻት ሰበብ ለእስር እየዳረጉዋቸው ይገኛሉ ያሉት የማዘጋጃ ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች የወያኔ ወዳጅ የሆነው ሼህ ሙሀመድ አላሙዲን የሀገሪቱ ሀብት የሆነውን የለገደንቢ ወርቅ ያለ አንዳች ቀረጥ እና ግብር እየጫነ ትንፍሽ ሳይሉ ከመቅረታቸውም በላይ በየቦታው ግንባር የሆኑ መሬቶችን እየወሰደ አጥሮ ለዓመታት ከማስቀመጥ ውጭ የሰራበት ነገር እንደሌለ እያወቁ ዝምታን የመረጡት እነ ኩማ ደመቅሳ ዛሬ በሌሎቹ ሪል እስቲት አልሚዎች ላይ አስደንጋጭ እርምጃ መውሰዳቸው የሚሳዝን እና የሚያሳፍር ነው ሲሉ እነዚሁ ባለሀብቶች በምሬት እየገለፁ ናቸው::

ምርቱን ከግርዱ ስንዴውን ከእንክርዳዱ መለየት ግድ የሚል ቢሆንም አሁን እየታየ ያለው የነኩማ ደመቅሳ ዘመቻ ለህዝብ ተቆርቁረው ለሀገር አስበው ሳይሆን ቀጣይ የአፈና አገዛዛቸውን አጥበቀው ለመሄድ እንዲያመቻቸው በግል ተሰርተው የሚሸጡትን መኖሪያ ቤቶች ቀስ በቀስ በቁጥጥር ስር አድርገው ለማስቀረት የታለመ መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የተሰጣቸውን መሬት አጥረው ያስቀመጡና ያላለሙ ብሎም አየር በአየር  ሸጠው ዛሬ አንቱ የተባሉ ቱጃሮች መኖራቸው አይካድም ያሉት ምንጮቹ  እነሱ እነማን ናቸው ተብሎ ቢጠየቅ እና ቢመረመር የወያኔ ቡድን አቀንቃኝ ብሎም ከበረሀ የመጡ የታጋይ ነን ባዮች መሆናቸው ቁልጭ ብሎ ይታወቃል ሲሉም አስረድተዋል፡፡

በተለይ በ1997 ዓ.ም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት በሙሉ እስከ ግልገል  ካድሬዎች አንድ ሰው እስከ 4 ሺህ ካሬ ሜትር ድረስ ቦታ ወስዶ እንደነበርና ይሄንን ቦታ መልሰው ቸብችበው ዛሬ ትልቅ ሀብታም ለመሆን የበቁ መሆናቸው እየታወቀ ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ በገዛ ሀብታቸው መሬት ገዝተው በሪል እስቴት ስራ ተሰማርተው ያሉትን እየነጠቁ ማባረራቸው የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ አይን አውጣነት መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ ዛሬ የቤት ችግር ህዝቡን እግር ከወርች አስሮ አላላውስ ከማለቱም በላይ በልማት ስም ህዝቡ ከነ ቤተሰቡ የጎዳና ተዳዳሪ እየሆነ ባለበት ወቅት መሬት እየቀሙ ለራሳቸው ማግበስበስ መጀመራቸው እጅግ አሳፋሪ ነው ሲሉም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በእህት ወንድሞቻቸው ብሎም በዘመዶቻቸው ስም መሬት ሸንሽነው ሲከፋፈሉ የነበሩት የወያኔ ባለስልጣናት ሀብት ምንጩ ይመዝገብ ተብሎ የወጣውን አዋጅ ከታቀደው ግዜ አራት ዓመት በላይ እንዲዘገይ አድርገው እነሱ ሸጠው ከጨረሱ በሁዋላ ዛሬ አዋጁን አፅድቀው ቢቀመጡም ተግባራዊ ለማድረግ ተቸግረው እንዳሉ የጠቆሙት ምንጮቹ ጉዳዩ ተድበስብሶ እንዲቀር እና የህዝቡን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ተብሎ የወያኔ ደጋፊ ያልሆኑ አልሚ ባለሀብቶች ብቻ እየተመረጡ መሬት መነጠቃቸው እያነጋገረ ይገኛል ብለዋል፡፡

በቢሮክራሲ ችግሮች ጭምር ተተብትቦ መፍታት ያልቻለው የኩማ ደመቅሳ ካቢኔ የራሱን ችግር መልሶ ባለሀብቶቹ ላይ ቆልሎ ከማስቀመጡም በላይ ሌባ እያለ ጣቱን እየቀሰረባቸው መገኘቱ የሚያሳዝን ነው ያሉት ባለሀብቶቹ በውጭ ሀገር ለዓመታት ሰርተን ያገኘናትን ገንዘብ በሀጋራችን እንስራበት ብለን ብንመጣም በአንድ ሀገር ሁለት አሰራር በመኖሩ እኛ የበይ ተመልካች ልንሆን ችለናል ሲሉም በሀዘን ሲገልጹ ተደምጠዋል፡፡

እንደ ደርግ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም ሰሞኑን ነጋዴዎችን የእናት ሀገር ደም መጣጭ እያለ መስደብ የጀመረው የአዲስ አበባ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ  በሊዝ መሬት ገዝተው የነበሩ እና በቤት ስራ ላይ ተሰማርተው ባሉት ባለሀብቶች ላይ የተወሰደው እርምጃ የወቅቱን ሁኔታ ያላገናዘበ መሆኑን የጠቆሙት ባለሀብቶቹ ዛሬ የብረት ፤የሲሚንቶና ሌሎች ግብአቶች ዋጋቸው ጣራ ላይ በነካበት ወቅት ችግራችሁ ምንድነው ብለው ሳይጠይቁ በግብታዊነት እርምጃ መውሰዳቸው የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን  የሚያሳፍር ሀገርን እና ህዝብን የሚጎዳ ነገሮችን አዙሮ ካለማየት የመነጨ ነው ሲሉም በቁጭት ይገልጻሉ፡፡

ለዘመናት ከኖረበት ቀዬ በልማት ስም ህዝቡን እያፈናቀሉ ለጎዳና ተዳዳሪነት እየዳረጉ ያሉት እነ ኩማ ደመቅሳ በቅርቡ ለሸራተን አዲስ ሆቴል ማስፋፊያ ተብሎ ከቦታቸው እንዲነሱ የተደረጉትን ሰዎች በቂ ያልሆነ ካሳ በመስጠታቸው ተቃውሞ ለማሰማት ቢሞክሩም በፖሊስ ቆመጥ እየተደበደቡ እንዲበተኑ ከማድጋቸውም በተጨማሪ ለእስር መዳረጋቸው የሚታወስ ሲሆን ህዝቡ ባላመነበት እና ባልፈለገው መንገድ ወያኔዎች ለራሳቸው ሰዎች ሲሉ የሚወስዱት እርምጃ መሆኑን የሚያመላክት ነው ብለዋል::

ከዜጎች ይልቅ ለውጭ ሀገር ዜጋ ባለሀብቶች እያሸረገደ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ዛሬ ከአዲስ አበባ ከተማ ጀምሮ እስከ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ድረስ እጅግ ግዙፍ እና ሰፋፊ መሬቶችን በትንሽ ዋጋ እያደላቸው ከመሆኑም በላይ ስራ ሳይሰሩበት አጥረው እያስቀመጡ ባሉት ላይ እርምጃ ሳይወስድ በኢትዮጵያውያኑ ባለሀብቶች ላይ እየወሰደ ያለው ከፖለቲካ ስጋት የመነጨ ሊሆን እንደሚችልም ግምታቸውን የሚሰነዝሩ አልጠፉም::

ሰሞኑን የተጀመረው የሪል እስቴት አልሚዎች መሬት ነጠቃ ወደ ግለሰብ ደረጃ ዝቅ ብሎ በየመንደሩ ውስጥ ከ50 ዓመት በፊት ጀምሮ በይዞታነት ይዘውት የነበረውን መሬት ሁሉ እየነጠቀ እንደሚወርስ የማዘጋጃ ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጠቁመዋል::

በሌላ ዜና የአቡነ ጳውሎስ ቀኝ እጅ የነበረውና በሲኖዶሱ ውሳኔ ከስልጣኑ የተባረረው ሊቀ መዕምራን ሙጬ የተባለው ግለሰብ ድንገት ሳይታሰብ ወደ ውጭ ሀገር መኮብለሉ ተጋለጠ::

አባ ሳሙዔል የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው በሰሩበት ዘመን የቤተክርስቲያንዋ ገንዘብ ተመዘብሮዋል ብለው አባ ገብረ መድህን እንዲጣራላቸው ለሲኖዶሱ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ተንተርሶ በተደረገው ኦዲት በአባ ሳሙኤል ላይ የቀረበው ሁሉ ውድቅ ሆኖ በተገላቢጦሹ ከውጭ ሀገር ያስመጡት ወጠጤ ጎረምሳ የሆነው ሊቀ መዕምራን ፋንታሁን ሙጬ የተባለው ግለሰብ 42 ሚሊዮን ብር መዝብሮ በሰነድ የተረጋገጠበት በመሆኑ በህግም እንዲጠየቅ ለአባ ጳውሎስ ሪፖርቱ በመቅረቡ ግለሰቡ ከሀገር በአስቸኳዋይ እንዲወጣ ማድጋቸው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋልጦዋል::

የአዲስ አበባን አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደሮች እያስፈራራና ከስራቸው አንዳንድ ካድሬዎችን መድቦ ከህዝበ ክርስቲያናት የሚገኘውን ገንዘብ ሲመዘብር እና ለአባ ገብረ መድህን ሲያካፍል የቆየው ይሄው ግለሰብ ከስልጣኑ እንዲባረር እና በህግ እንዲጠየቅ ሲኖዶሱ በወሰነ ማግስት ከአባ ገብረ መድህን ጋር በመመሳጠር ሌሊቱን አምልጦ መሸሹን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ሊቀ መዕምራን ፋንታሁን ሙጬ የተባለው ግለሰብ ወደ ኦስትሪያ እንደተሸኘ የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮች በተደረጉት ስብሰባዎች ላይ እንዲገኝ በተደጋጋሚ ግዜ ቢጠራም ሳይገኝ ቀርቶ ይልቁንም በየቤተክርስቲያኑ እየዞረ ገንዘብ አምጡ እያለ የጻፋቸውን ደብዳቤዎች እየተዘዋወረ ሲለቃቅምና ሲያቃጥል የቆየ ቢሆንም ነገሩ እየከበደና አባ ገብረ መድህንን ጭምር የሚያጋልጥ በመሆኑ ከእሳቸው ጋር በመመሳጠር ከሀገር ወጥቶ ሊጠፋ እንደቻለ ጥቆማው አብራርቶዋል::

አባ ገብረመድህን በሲኖዶሱ የተወሰነውን ውሳኔ በሚፃረር መልኩ ውስጥ ውስጡን እየሰሩ ከመሆኑም ባሻገር በስልጣን ላይ እያለ በህዝብ ገንዘብ ሲጫወት የነበረው ፋንታሁን ሙጬ ተይዞ ለህግ እንዲቀርብ ተብሎ የነበረ ቢሆንም እሳቸው እና የደህንነት ሰራተኞቻቸው ብቻ በሚያውቁት መንገድ በቦሌ በአውሮፕላን ጣቢያ በኩል ለስራ ጉዳይ በሚል ህጋዊ ደብዳቤ ፅፈውለት ሊወጣ እንደቻለ ከቤተክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

ከዚህ በተጉዋዳኝ ሲኖዶሱ የአባ ገብረ መድህን ሐውልት እና ምስል በየአደባባዩ መሰቀል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ጋር የማይሄድ..... እራስን እንደ ፖለቲከኛ መቁጠር ከአንድ አባት የማይጠበቅ ነው በማለት ኮንኖ በአጭር ግዜ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ እንዲቀለበስ ሰሞኑን ዘመቻ መጀመራቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ምንም እንኩዋን ሲኖዶሱ በሙሉ ድምጽ ወስኖ በአጭር ግዜ ውስጥ እንዲፈጸም ያለ ቢሆንም አባ ገብረ መድህን በቦሌ መድሀኒዓለም የተሰራውን ሐውልት እንዳይፈርስ በራሳቸው ሰዎች ውስጥ ውስጡን ተቃውሞ እንዲነሳና ወደ ብጥብጥ እንዲያመራ እያደረጉ መሆኑ ተጋልጦዋል::

ከጥቅምት 12 ቀን እስከ ጥቅምት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ሲኖዶሱ ያደረገውን ጉባዔና የደረሰበትን ውሳኔ ተንተርሶ መግለጫ እንዲወጣ ተወስኖ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ፅፈው አባ ገብረ መድህን እንዲያነቡ የተወሰነ ቢሆንም አባ ገብረ መድህን የሲኖዶሱ ውሳኔን ወደ ጎን በመተው አባ ገሪማ ጽፈው የሰጡዋቸውን በማቅረባቸው ከፍተኛ ተቃውሞ መቀስቀሱ ተሰማ::

ብዙ ታሪካዊና ወሳኝ ጉዳዮችን ወስኖ ያፀደቀው የሲኖዶሱ ጉባዔ መጠናቀቂያው ላይ የሲኖዶሱ መግለጫ ተብሎ በወያኔ ራዲዮና ቲሌቪዥን እንዲተላለፍ የተደረገው ሲኖዶሱ ከሰጣቸው ፅሁፍ ሌላ ተቀይሮ በመቅረቡ ጳጳሳቱ እጅግ ከማዘናቸውም በላይ ቁጣ መቀስቀሱ ከደረሰን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

በስብሰባው ላይ የተገኙት ጳጳሳት አባ ገብረመድህን በሰጡት መግለጫ እጅግ የተበሳጩ መሆኑን ያወቁት እኚሁ ሰው አይናቸውን በጨው አጥበው ጳጳሳቱን ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ በማለት እንደጠየቁም ምንጮቹ አስረድተዋል::

የሲኖዶሱ ውሳኔ በ20 ቀናት ውስጥ ሁሉም ነገር ተግባራዊ መሆን እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም ከአባ ገብረ መድህን ጋር ቅርብ ትስስር አላቸው የሚባሉት የጠቅላይ ቤተክህነት ስራ አስኪያጅ አቡነ ፍሊጶስ በተወሰነው ውሳኔ ቃለ ጉባዔ ላይ ሳይፈርሙ በመዘግየታቸው እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ እንደሌለ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አብራርተዋል::

ከአባ ገብረ መድህን ጋር እጅግ የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው የሚነገርላቸው አቡነ ፍሊጶስ ሐውልቱ እንዳይፈርስ ከሚታገሉት አንዱ በመሆናቸው ቃለ ጉባዔው ላይ ሳይፈርሙ የቆዩ ሲሆን ይህ ዘገባ እስከ ቀረበበት ሰዓት ድረስ ፊርማቸውን እንዳላኖሩ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

አባ ገብረ መድህን እንደ ሌሎቹ ዓመታቶች እንደልብ ሳይፈነጩ በህዝበ ክርስቲያኑ እና በሊቃውንቶች ላይ የሰሩት በደል ተጋልጦ ከመውጣቱ በተጨማሪም ያቀረቡት አቤቱታ እና ስሞታ በሙሉ ውድቅ የሆነባቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ

በተለይ አቡነ ሳሙዔልን ለመጉዳት ብለው የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከትን ለአራት ዞን ለመከፋፈል ያቀረቡትን ጥያቄ ሲኖዶሱ እስከ ዛሬ እንደነበረው በአንድ ጳጳስ ብቻ እንዲተዳደር ብሎ በሙሉ ድምጽ ውድቅ እንዳደረገባቸው ምንጮቹ ገልጸዋል፡፡

አባ ገብረ መድህን በዘንድሮው ጉባዔ ላይ ከፍተኛ ዘለፋና ወቀሳ ብሎም ትችት የደረሰባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ሙሉ ለሙሉ ድጋፍ ያጡ በመሆኑ የራሳቸውን ሰዎች ለማሰባሰብ ሲሉ ሌሎች 18 ጳጳሳት እንዲሾሙ ለሲኖዶሱ ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ሲኖዶሱ ጥያቄውን ሳይቀበል በሙሉ ድምጽ ውድቅ አድርጎባቸዋል ያሉት ምንጮቹ በተለይ አዲስ የቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ተቀርፆ ይውጣ የሚለውን የአባ ገብረ መድህንን ጥያቄም አሁን ያለውንስ መቼ በቅጡ ተግባራዊ አደረግነውና ነው ሌላ እንዲወጣ የተጠየቀው በማለት ሲኖዶሱ አሳፍሮ ውድቅ አድርጎባቸዋል ሲሉ ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ከአባ ገብረ መድህን ጋር እጅግ የተለየ ቀረቤታ ያላት እጅጋየሁ በየነ የተባለችው ባልቲት ከዚህ ቀደም በ3 የተለያዩ ሀገራት ሐውልታቸውን እናቆማለን..... ለግላቸው የሚንቀሳቀሱበት አውሮፕላን እንገዛላቸዋለን.....እያለች በድፍረት እና በይፋ ስትናገር እንደነበር ጉባዔው ላይ ተነስቶ የተወያዩበት ሲሆን ሲኖዶሱም እንኩዋን ተጨማሪ ሊሰራ ቀርቶ አሁን የተሰራውም ተገቢ አይደለም ስለዚህ ግለሰቡዋ ለሰጠችው መግለጫ ማስተባበያ እንድትሰጥ ሲል በሴትዮዋ ላይ ተጨማሪ ውሳኔ አስተላልፎዋል ብለዋል፡፡

በዚሁ ጉባዔ ላይ አንደኛው ጳጳስ ግለሰቡዋ (እጅጋየሁን ማለታቸው ነው) የየደብር ኃላፊዎችን ሁሉ ከስራ አባርራለሁ እያለች የምትደነፋ ፊርማና ማሕተም ከየት እንደምታመጣ ሳይታወቅ በራስዋ ስልጣን የቤተክህነት ሰተራተኞችን እንዳሻት ስትሾምና ስትሽር የኖረች ናት በማለት የገለፁ ሲሆን ከእንግዲህ ይህ ጣልቃ ገብነት እንዲወገድ እና አቡነ ጳውሎስም ይሄን ሁኔታ እንዲያርሙ ከመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ጋር እንደተነገራቸው ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ከመንፈሳዊ እምነት ይልቅ አብዮታዊ ዲሞክራሲ......ከእምነት አባትነት ይልቅ የካድሬነት ስራ.....ከፆም ፀሎት ይልቅ ፌሽታ .....የሚበልጥባቸው አባ ገብረ መድህን ሲኖዶሱ የሰጠውን ትዕዛዝ በፊርማቸው አጽድቀው የተቀበሉት ቢሆንም ተግባራዊ እንዳይሆን ውስጥ ውስጡን እየሰሩ ያሉት ሴራ እየገፋ ከሄደ በቤተክርስቲያኑዋ ውስጥ ከፍተኛ ብጥብጥ ለነሳ እንደሚችልም ምንጮቹ ስጋታቸውን ይገልጻሉ፡፡